# ግብፆችን ማን ይምከርልን?

ኢዛና ዘመንፌስ 01/27/14

ታህሳስ 26ና 27፣ 2006 ዓ/ም ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብፅ በውሃ ሀብት ሚኒስትሮቻቸው አማካኝነት የተሳተፉበትን የሶስትዮሽ ድርድር ካርቱም ውስጥ ማካሄዳቸው አይዘነጋም። ይሄኛው የምክክር መድረክ ቀደም ሲል በሀገራቱ መካከል ከተደረጉት መሰል ውይይቶች ሁሉ የተሻለ መግባባት የተስተዋለበት እንደነበርም ተገልጿል።

ይሁን እንጂ አሁንም ከግብፅ በኩል የሚንፀባረቀው ግትር አቋም ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ለምትገነባው የህዳሴ ግድብ ጤናማ አመለካከት እንደሌላቸው የሚጠቁም ነው ማለት ይቻላል። ከዛሬ ግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት በአፍሪካውያን ህዝቦች ሀብትና ንብረት አዛዥ ናዛዥ የነበሩት የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የፃፉትንና እጅግ በጣም ቅጥ ያጣ ኢፍትሐዊነት ጎልቶ የሚስተዋልበትን የቅኝ ግዛት ዘመን ውል የሙጥኝ ማለት የመረጡም ይመስላሉ፤ ግብፆች።

የዚህ ዓይነቱ ያረጀና ያፈጀ (ጊዜ ያለፈበት) ብልጣብልጥነት ደግሞ ይሉኝታቢስነታቸውን ገሀድ አውጥቶ ለትዝብት ይዳርጋቸው እንደሁ እንጂ በአሁኑ ዓለም አቀፋዊ እውነታ ፈፅሞ ተቀባይነት አይኖረውም። ስለዚህ ግብፃውያኑ ወንድሞቻችን ዛሬ ላይም እንደዘመነ ቅኝ አገዛዝ “አንተ አብራ እኔ ልብላ” ከሚል ፍርደ ገምድልነት በመነጨ ኢ-ፍትሐዊ ፖሊሲ ለመቀጠል ማሰብ እንደማያዋጣና ወቅቱ ለሀገራት የጋራ ጥቅም የሚበጅ የሰጥቶ መቀበል መርህን የሚጠይቅ እንደሆነ ይገነዘቡልን ዘንድ ደግመን ደጋግመን ከመምከር አንቦዝንም። አለበለዚያ ግን “ከባልሽ ባሌ ይበልጣልና ሽሮ አበድሪኝ” እንዳለችው ሴት በአጉል ብልጣብልጥነት “ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር እየቆረጡ መኖር ይቻላል” ብለው የሚያምኑ ያስመስልባቸዋል፡፡

ምክንያቱም ለናይል ተፋሰስ ሰማኒያ አምስት ከመቶ የውሃ መጠን እይበረከተች በእስከ ዛሬው ታሪኳ የበይ ተመልካች ሆና የቆየችው ኢትዮጵያ አሁን በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገነባው የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብም ከታችኞቹ ሀገራት ጋር የሚያቃቅር ተፅእኖ የማይፈጥርበትን ቅደመ ሁኔታ በማመቻቸት ረገድ ብዙ እርቀት መጓዟን ዓለም የሚያውቀው ጉዳይ ነውና። በግልፅ አነጋገር ሀገራችን ኢትዮጵያ ከፈርጀ ብዙ ድህነት ለመውጣት ስትል የምታካሂደው መጠነ ሰፊ የልማት ንቅናቄ አካል የሆነውን የህዳሴ ግድብ ለምን ትገነባለች የሚል ቅሬታ ማቅረብ በራሱ ያስተዛዝባል ማለቴ ነው።

ይህ የግብፆች ግትርነት የሚያረገግጥልን እውነታ ደግሞ በቀደመው ታሪካችን ኢትዮጵያውያን በዓባይ ወንዝ የውሃ ሀብታችን የመጠቀም ህጋዊና ተፈጥሯዊ መብታችንን ተነፍገን እንድንኖር ለማድረግ እክል ይፈጥሩብን ነበር የሚባለው ነገር ተራ ሐሜት አለመሆኑን ነው።  መቸስ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በዓባይ ወንዝ ላይ መገንባቱ ለተፋሰሱ የግርጌ ሀገራት ህልውና አሳሳቢ ስጋት የሚፈጥር ቢሆን ኖሮ ሱዳንም አሁን የያዘችውን ቀና አቋም ባልያዘች ነበር።

ጥያቄው ፍትሐዊ የውሃ ክፍፍልን መሰረት ላደረገ የጋራ ተጠቃሚነት መርህ የመገዛት ፍቃደኝነት የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ነው እንጂ፣ የህዳሴውን ግድብ ግንባታ ሱዳን ደግፋ ግብፅ የምትቃወምበት ሌላ ምክንያት ሊኖር አይችልም። ስለዚህ ሱዳናውያኑ ጎረቤቶቻችን ላሳዩት የአፍሪካዊ ወንድማማችነት መንፈስ መመስገን የሚገባቸውን ያህል ግብፆችንም ስህተታቸውን አርመው ወደቀናው መንገድ እንዲመጡ የሚመክር ወዳጅ ዘመድ ያስፈልጋቸዋል ባይ ነኝ ።

ሰሞኑን ካርቱም ውስጥ በተካሄደው የሶስቱ ሀገራት ስብሰባ ኢትዮጵያን ወክለው የተሳተፉት የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴሩ ክቡር አቶ አለማየሁ ተገኑ ለዚሁ ጉዳይ ወደሱዳን ከማምራታቸው በፊት ዓርብ ታህሳስ 18 ቀን ታትሞ ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር አጭር ቃለምልልስ ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡ በዚህ ቃለ ምልልስ "ኢትዮጵያ ግብፆች ከልብና በእውነተኛ መንገድ ወደትብበሩ እንዲመጡ ትፈልጋለች" ብለው እንደነበር አይዘነጋም። ሚኒስቴሩ ታህሳስ 26ና 27 በተካሄደው የምክክር መድረክ ተሳትፈው ሲመለሱ ለመገናኛ ብዙሃን ሰዎች የሰጡት ማብራሪያ ግን ከዚህ የኢትዮጵያ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም አልነበረም፡፡ የግብፅ መንግስት

ከሁለቱ ሀገራት (ከኢትዮጵያና ከሱዳን) የተለየ ግትር አቋሙን የሙጥኝ እንዳለ ነበር የገለፁት።

ሰሞኑን ካርቱም ላይ ለሁለት ቀናት በተደረገው የሶስትዮሽ ውይይት የሀገራቱን የውሃ ሀብት ሚኒስቴሮች ጨምሮ በርካታ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ባለሙያዎችም እንደተሳተፉበትና አንፃራዊ የመግባባት መንፈስ የተስተዋለበት እንደነበር መገለፁ እንዳለ ሆኖ፣ በተለይም ግብፆች ያቀረቡት መከራከሪያ ቅንነት የጎደለው ስለመሆኑ ግን መረዳት አያዳግትም። ከግብፅ በኩል ቀረበ የተባለው ጥያቄ ቀደም ሲል ሶስቱ አገራት ከተስማሙበት ከሶስቱ ሃገራት የተወጣጣ የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ የቀረበውን ምክረ ሃሳብ አተገባባር ለመከታተል ከሚቋቋመው የባለሞያዎች ቡድን በተጨማሪ የህዳሴውን ግድብ የግንባታ ሒደት የሚመረምር ዓለም አቀፋዊ የኤክስፐርቶች ፓናል እንቅጠር የሚል ነበር፡፡ ኢትዮጵያና ሱዳን ይህን አቋም ሳይቀበሉት ቀረተዋል። ይህ የግብፅ አቋም ይድርድሩን ሂደት ከማጓተትና ከማደናቀፍ በስተቀር ፋይዳ የሌለው መሆኑ ነው የተገለፀው፡፡

በእርግጥም ደግሞ እንደዚህ ዓይነቱን አላስፈላጊና ላለመገባባት ሲባል ብቻ የቀረበ ደንቃራ የሚመስል የግብፆች ሃሳብ መቀበል ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም ጉዳዩን እንዳዲስ ለማወሳሰብ ከመፈለግ የመነጨ ቅንነት ማጣት ካልሆነ በስተቀር ከሶስቱ ሀገራት አቅም በላይ ነው የሚባል አንድም አሳሳቢ ችግር በሌለበት ሁኔታ ዓለም አቀፋዊ ጣልቃገብነትን የሚጋብዝ ጥያቄ ማንሳት ፈፅሞ አያስፈልገም።

እንዲያውም እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ግብፃውያኑ አሁን ያቀረቡት ሃሳብ እነርሱ ዛሬም ድረስ “የአፍሪካውያን ችግር ያለፈረንጆች ጣልቃ ገብነት አይፈታም” የሚል እምነት እንዳላቸውና የቀድሞ ቅኝ ገዢዎቻቸውን ረጃጅም እጆች ከመጠበቅ የመነጨ ተልካሻ ምክንያት ለመደርደር እየሞከሩ እንደሆነ ያሳብቅባቸዋል። ግብፆች የዓባይ ወንዝ መነሻ የሆነችው ኢትዮጵያ ታላቁን የህዳሴ ግድብ መገንባት ከመጀመሯ በፊት ለመላው የናይል ተፋሰስ ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነት ይበጃል ብላ ያመነችበትን የትብብር ማዕቀፍ በአፍሪካዊ የወንድማማችነት መንፈስ ከማርቀቅ እስከ ማፅደቅ የዘለቀ የአስተባባሪነት ሚና እንደተጫወተች ሳያውቁ ቀርተው አይደለም ።

ሱዳንን ጨምሮ ሌሎቹ ባለድርሻ ሀገራት የናይል ተፋሰስን በፍትሐዊ መንገድ ለጋራ ጥቅም የማዋሉ ጉዳይ ከመቸውም ጊዜ በላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና ለነገ የማይባል ስለመሆኑ የተገነዘቡትም እኮ የትብብር ማዕቀፉን ከማርቀቅ እስከማፅደቅ በነበረው የአስር ዓመት ጉዞ ነው። እናም ጉዳዩን በተመለከተ እያንዳንዱ የተፋሰሱ አባል ሀገር  ለትብብር ማዕቀፉ መጠናከር የየራሱን ገንቢ አስተዋፅኦ ከማበርከት ያልቦዘነው ለጋራ ዘላቂ ጥቅም የሚበጀው ቀና መንገድ የትኛው እነደሆነ በቂ ግንዛቤ ከመጨበጡ የተነሳ ነው፡፡

በመሆኑም የዓባይ ተፋሰስን የውሃ ሀብት አፍሪካዊ ወንድማማችነትን መሰረት ባደረገ ፍትሃዊ ክፍፍል ለጋራ ጥቅም ማዋል የሚያስችለው ማዕቀፍ ስራ ላይ እንዲውል መስማማቱን በፊርማው ካላረጋገጡ ጥቂት የተፋሰሱ ሃገራት መሃከል ቀዳሚዋ ግብፅ ናት ማለት ይቻላል። ግን እስከመቼ ይሆን ግብፃውያኑ ወንድሞቻችን ከዚህ ሽሽተው ከማያመልጡት ነባራዊ እውነታ ለማፈላለግ መሞከራቸውን የሚገፉበት? እንደኔ እምነት ግን አሁን በስልጣን ላይ ያለውን የግብፅ መንግስት የሚመሩት ፖለቲከኞች ራሳቸው የትብብር ማዕቀፉን የመፈረም ታሪካዊ ሃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል።

ግብፆች ዛሬ እንኳን ካረጀ ካፈጀው የዜሮ ድምር አስተሳሰባቸው በመላቀቅ የዓባይን ውሃ ለጋራ ጥቅም ማዋል የሚቻልበትን የፍትሃዊነት ጥያቄ ይቀበሉ ዘንድ ሁነኛ መካሪ ያሻቸዋል የምልበት ዋነኛ ምክንያትም ወቅቱ ከዘመነ ቅኝ አገዛዝ ፈጽሞ የተለየና አፍሪካውያን ህዝቦች በአዲስ የታሪክ ምዕራፍ ላይ የሚገኙበት መሆኑን ስለምገነዘብ ጭምር ነው። ስለዚህ ግብፃውያኑ ወንድሞቻችንም ከህዳሴው ዘመን የአፍሪካዊነት ጥያቄ ማፈግፈግና አላስፈላጊ ኪሳራ የሚያስከትል ግትርነትን የሙጥኝ ማለት እንደማይጠበቅባቸው ይሰማኛል።

ምናልባት ግብፃውያኑ ከዚህ ቀና መንገድ ውጭ ሌላ አማራጭ የሚገኝ መስሎአቸው ከሆነ ግን ያአማራጭ ለነሱም ለኛም እንደማይበጅ ከወዲሁ መገመት አያዳግትም። ሰሞኑን አንዳንድ የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ውጤቶች የግብፅ ባለስልጣናት የህዳሴው ግድብ ግንባታ ሰላሳ ከመቶ ደርሷል የሚባለው ለፖለቲካ ትርፍ ነው እንጂ ገና ምኑም አልተነካ የሚል የግብፅ ባለስልጣናትን  ገለፃ አሰነብበውናል። በእርግጥም

ግብፆች የዚህ አይነት  አቋም ካላቸው ጉዳዩን በሃሰ ለግብፅ ሕዝብ ያልሆነ መረጃ በማቀበል ጉዳዩን ለርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ማግኛነት መሆኑን ያመለክታል።

ለምን ቢባል ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ ለመላው የሀገራችን ህዝቦች የዘመናት ቁጭት ምላሽ የሚሰጥ ታሪካዊ ፕሮጀክት እንጂ፣ ለአንድ ሰሞን የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈፀሚያነት ታስቦ የተወጠነ ግንባታ ባለመሆኑ የግንባታው ሂደት ለአንድ ቀን ያህል እንኳን ተቋርጦ አያውቅም። ስለዚህ ይህን እውነት አዛብቶ የማቅረብ  የግብፅ አቋም በወቅቱ እልባት ካልተበጀለት የሁዋላ ሁዋላ ውጤቱ እንደማያምር ደፍረን እንነግራቸው ዘንድ እንገደዳለን።

እኛ ኢትዮጵያውያን ከዚህ ቀደም ባሳለፍነው ረጅም ታሪክ “ አባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል” በሚል ቁዘማ የበይተመልካች ሆነን መቆየታችንን ስናስበው ቁጭቱ የሚያንገበግበን አልበቃ ብሎ፣ አሁንም የዚያን ዓይነቱ አሳዛኝ ሁኔታ እንዲቀጥል የምንፈቅድ ህዝቦች ከመሰልናቸው ግብፆች በእርግጥም አያውቁንም ማለት ይቻላል። በተለይም ደግሞ ዛሬ እንደሀገር በፈርጀ ብዙ የህዳሴ ጉዞ ላይ የምትገኘው ኢትዮጵያ ግድቡን ለተራ ፖለቲካዊ ትርፍ ማጋበኛነት ልትጠቀምበት ከማሰብ ነው የጀመረችው ብሎ መገመት አጅግ አደገኛ የስሌት ስህተት እንደሆነ ይሰማኛል።

ምክንያቱም አሁን ያለንበት ወቅት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የድህነትን አስከፊነት ከመቸውም ጊዜ በላይ የተረዳበትና አምርሮ ሊፋለመው የተነሳበት ነው። መላው የሀገራችን ህዝቦች የሚያካሂዱትን የፀረድህነተ ትግል ይበልጥ አጠናክሮ ማስቀጠል ይቻል ዘንድም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ የድል አድራጊነቱን አቅጣጫ የሚጠቁም አጥቢያ ኮከብ የመሆን ታሪካዊ ሚና ይጫወታል የመል እምነት ተፈጥሯል። ይህ ማለት ደግሞ በዓባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለው የህዳሴ ግደብ የዚችን ሀገር ህዝቦች መፃኢተስፋ የሚወስንና እንደየዓይናችን ብሌን የምንቆጥረው ታሪካዊ ሀብታችን እንጂ ለተራ የፖለቲካ አጀንዳ መጠቀሚያነት  የሚሰራ እንዳልሆነ የሚያስገነዝብ እውነታ ይመስለኛል።

እንዲህም ሆኖ ግን የግድቡ ግንባታ ሒደት የትኛውንም የዓባይ ተፋሰስ አባል ሀገር የሚያሳሰብ አንዳች አሉታዊ ተፅእኖ የማይፈጥርበትን አስተማማኝ ዋስትና

ባስቀመጠ ቅድመ ሁኔታ ላይ እንደተጀመረ ሌላው ቀርቶ ግብፆች ራሳቸውም የማይክዱት ነባራዊ ሀቅ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ የኃይል ማመንጫ ግድብ ለመገንባት ስንነሳ እንደዋነኛ ዓላማ ያስቀመጥነው ቁልፍ ጉዳይ የዓባይ ወንዝ የውሃ ሀብታችንን ተጠቅመን እንደሀገር በዓለም ህዝብ ታሪክ ፊት እንድናፍር አድርጎን ከቆየው ፈርጀ ብዙ ድህነት መላቀቅ ነው እንጂ ግብፅንም ሆነ ሌላ ማንኛውንም ወገን መጉዳት አይደለም።

ይህን ስናደርግም ቢሆን ግን ፍትሐዊ የውሃ ክፍፍልን መሰረት አድርጎ በሚፈፀምና የጋራ ተጠቃሚነትን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ እንደሆነ አስቀድመን ማስገንዘባችን ይታወቃል። እውነታው ይህ ስለመሆኑ ደግሞ እንኳንስ ኢትዮጵያ ሌሎቹ (ከግብፅ በስተቀር) የተፋሰሱ ባለድርሻ ሀገራት ጭምር በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከመግለፅ ቦዝነው አያውቁም። ታዲያ ግብፃውያኑ ወንድሞቻችን ምን የተለየ ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል…!?

የህዳሴው ግድብ ጉዳይ ያለቀለት ሆኖ ሳለ እነርሱ ብቻ እንደአዲስ አጀንዳ እያነሱ ውዝግብ የመፍጠር ሙከራ ሲያደርጉ የሚስተዋሉት ለምንድነው? ወይስ አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት በራሳቸው የውስጥ ችግር ከመጠመዳቸው የተነሳ ተረጋግተው ለመወሰንና ቁርጥ ያለ አቋም ላይ ለመድረስ አላመች ስላላቸው ይሆን ? የኢፌዲሪ መንግስት የውሃ፣ የመስኖና የኢነርጂ ሚኒስቴር ክቡር አቶ አለማየሁ ተገኑ "እኔ በዚህ ሃሳብ አልስማማም ነው" የሚሉት።

ሚኒስቴሩ ምክንያታቸውን ሲያብራሩም "አሁን ያለው የግብፅ ጊዜያዊ መንግስት ራሱ ፍቃደኝነቱ ቢኖረው ኖሮ የናይል ተፋሰስ ሀገራት የትብብር ማዕቀፍን ለመፈረም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ያጣል ብሎ ማመን ስህተት ነው ። ለምን እንዲህ እንደሚሆኑ እንጃ  ጉዳዩ ያን ያህል ከባድ አይደለም" ብለዋል በእርግጥም ደግሞ ክቡር የውሃ፣ የመስኖና የኢነርጂ ሚኒስቴሩ ልክ ናቸው።

ጥያቄው ፍትሐዊነትን መሰረት ላደረገ የጋራ ተጠቃሚነት ዝግጁ የመሆንና ያለመሆን ጉዳይ ነው እንጂ ግብፅን እንዳትፈርም ያደረጋት ምክንያት ወቅታዊው የውስጥ ችግሯ ሊሆን አይችልም በሚለው ብዙዎች ይስማሙበታል። በሌላ አነጋገር ጉዳዩን ሊያወሳሰቡት ካልፈለጉ በስተቀር በየትኛውም ጊዜና ቦታ ልባዊ

ስምምነታቸውን እንዳይገልፁ የሚያግዳቸው የውስጥ ችግር ይኖራል ብሎ ማመን ይከብዳል ።

“ግብፆቹ ሀገራቸው ባስተናገደችው  አብዮት ምክንያት ስላልተረጋጉ ነው እንጂ ዓባይን ላለማስገደብ ወደጦርነት ሊያመሩ ይችላሉ” ከሚል መላ ምት የመነጨ አስተያየት ሲሰጡ የሚደመጡ ወገኖች መኖራቸውም ግን መዘንጋት የለበትም። ነባራዊ እወነታው ጦርነትን እንዳማራጭ የመፍትሔ መንገድ ይወስዳሉ የሚለውን አያመለክትም፡፡

ክቡር የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ባሳለፍነው 2005 ዓ/ም ግንቦት ወር ላይ ግብፆች የጦርነት ዛቻ ስለመሰንዘራቸው አስተያየት ተጠይቀው “በእርግጥ የግብፅ መንግስት እንደዚያ ዓይነት ሃሳብ ካለው ይሄ ዕብደት ነው የሚመስለኝ! ምክንያቱም ጉዳዩ ለጦርነት ሊጋብዝ ይቅርና ምንም ያህል ችግር እንደማይፈጥርባቸው እነሱም ያውቃሉ . . .”  የሚል ምላሽ መስጠታቸው ይህን ያረጋግጣል። ያመ ሆነ ይህ ግብፆች ከአባይ ውሃ ፍትሃዊ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያዋጣቸው መንገድ በጋራ አጠቃቀም ላይ ተወያይቶ ስምምነት ላይ መድረስ ብቻ ነው።  ግብፅ ሰሞኑን ከሚታይባት ግትርነት ተላቃ ወደመግባባት እንድትመጣ መካሪ ያስፈልጋታል።እንግዲያው ማን ይምከራት?